የተከበራችሁ ጥሪ የተደረገላችሁ የክብር እንግዶች

የተከበራችሁ ጥሪያችንን አክብራችሁ በስብሰባው ላይ የተገኛችሁ የአዲስ አበባ ከተማ ኑዋሪዎች

በቅድሚያ በራሴና በፓርቲው ስም እንኳን ደህና መጣችሁ እያልኩ፣ ውድ ጊዜያችሁን ሰውታችሁ ከእኛ ጋር ለመወያዬት በዚህ ስብሰባ ላይ በመገኘታችሁ በቅድሚያ ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡ የዛሬው ስብሰባችን ዋና ዓላማ በአገራችን ወቅታዊ ሁኔታዎች፣ በፓርቲያችን የሦስተኛ አማራጭነት ሚናና በሚቀጥለው የ2002 ብሔራዊ ምርጫ ዝግጅት ዙሪያ መወያየት ቢሆንም ስብሰባው እኛ ተናጋሪ እናንተ አድማጭ እንድትሆኑ ሳይሆን በዋናነት የእናንተን ጥያቄ፣ አስተያዬት፣ ምክርና ቅሬታ ጭምር ለማዳመጥ ተብሎ የተዘጋጀ መድረክ ነው፡፡

ሁላችሁም እንደምታውቁት ከምርጫ 97 በኋላ ኢዴፓ እንዲህ ዓይነት ሕዝባዊ ስብሰባ ሲያዘጋጅ ይህ የመጀመሪያው ነው፡፡ ምርጫ 97ን ተከትሎ በአገራችን በተፈጠረው የፖለቲካ ቀውስ ምክኒያት አጠቃላይ ሠላማዊ ትግሉ ቀላል የማይባል ችግር ስለገጠመውና በተለይም ፓርቲያችን ኢዴፓ ለሠላማዊ ትግሉ ደህንነትና ቀጣይነት ሲል በወሰዳቸው ከሌሎች ፓርቲዎች የተለዩ አቋሞች ምክኒያት የተቀነባበረ የአሉባልታ ዘመቻ ሠለባ እንዲሆን በመደረጉ ለአለፉት አራት ዓመታት እንዲህ አይነቱን ሕዝባዊ ስብሰባ ጠርቶ የሰከነ ውይይት ለማድረግ ሳይችል ቀርቷል፡፡ በዚህ እረገድ የተከሰተው ችግር ሙሉ በሙሉ ተወግዷል ሊባል ባይችልም ምርጫ 97ን ተከትሎ በተፈጠረው የፓረቲዎች የአቋም ልዩነት የማን አቋምና ውሳኔ ትክክል እንደነበር ጊዜና ሂደት መልስ እየሰጡ በመምጣታቸው ፓርቲያችን ኢዴፓም በዛሬው እለት ይህንን ሕዝባዊ ስብሰባ ለማካሄድ በቅቷል፡፡ ከዚህ በኋላም ተመሳሳይ ድርጅታዊ አንቅስቃሴዎችን በመላው አገሪቱ የበለጠ አጠናክሮ ለመቀጠል ፓርቲያችን በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

ኢዴፓ ለአለፉት አራት አመታት ያለፈበት ሂደት እጅግ አስቸጋሪና ፈታኝ የነበረ ቢሆንም ከሂደቱ፣ ከሌሎችም ሆነ ከራሱ ስህተቶች ብዙ ተምሯል፡፡ በዚህ ሂደት የአገራችን የፖለቲካ ችግሮች እጅግ ውስብስብና ጥልቅ ከመሆናቸውም በላይ ችግሮቹም በአንድ በኩል ከገዥው ፓርቲ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከእራሳችን ከተቃዋሚ ፓርቲዎችና ሁላችንም ከፈለቅንበት ህብረተሰብ የማህበራዊ ኢካኖሚ የዕድገት ደረጃ የሚመነጩ ስለመሆናቸው ቀደም ሲል የነበረንን አመለካከት የበለጠ የሚያጠናክር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ ሂደት እኛ ከራሳችንም ሆነ ከሌሎች ስህተት መማር የቻልነውን ያህል ገዥው ፓርቲ፣ ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ሆኑ ሕዝቡ በአንፃራዊነት የዬበኩላችንን መማር ብንችል ለወደፊቱ የአገሪችን የፖለቲካ ሂደት ጠቃሚ እንደሚሆን እንገነዘባለን፡፡ በአንዳንድ የፖለቲካ ኃይሎችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ግምት ኢዴፓ ከዚያ ሁሉ የአሉባልታ ዘመቻ አገግሞና እንደገና አንሠራርቶ በአገሪቱ የፖለቲካ ሂደት ይቀጥላል ተብሎ አልታሰበም ነበር፡፡ ነገር ግን ኢዴፓ ፖለቲካው ሞቅ ደመቅ ባለበትና ደጋፊ በበዛበት ወቅት ብቻ ሳይሆን ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታዎች በተከሰቱበት፣ ተቃውሞ፣ ሃሜትና ውግዘት በበዛበትም ወቅት ለቆመለት መርህና ዓላማ ታማኝ ሆኖ በፅናት መቀጠል የሚችልና በክፉ ቀንም ህዝቡን ጥሎ ዘወር - የማይል የአቋም ፓርቲ መሆኑን ከመቼውም ጊዜ በላይ አረጋግጧል፡፡ ይህ አቋማችን በአሁኑ ወቅት እያራመድነው ከምንገኘው የሦስተኛ አማራጭነት ሚናችን ጋር በተያያዘ ወደ ኋላ ሊመለስ በማይችልበት ደረጃ የበለጠ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

ስለአገራችን ፖለቲካ በታሪክ ስናነበው ከኖርነውና እኛም የሂደቱ አካል በመሆን በተግባር ካገኘነው ተመክሮ በመነሳት እስካሁን ከነበረው በጭፍን የመቃወምና በጭፍን የመደገፍ የፖለቲካ ባህላችን በተለዬ አገራችን አዲስና ምክኒያታዊ የሆነ ሦስተኛ የፖለቲካ አማራጭ ያስፈልጋታል ብለን አምነናል፡፡ የአገራችንን የፖለቲካ ሁኔታ እስካሁንም ሆነ አሁን በውል እየተከታተለ ለሚገኝ ለማንኛውም ሰውም የሦስተኛ አማራጭነት ሚናችንን ምንነትና አስፈላጊነት ለመረዳት ብዙም የሚያስቸግር አይሆንም፡፡

በወቅቱ የአገራችን ፖለቲካ፤

ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት - ከጭፍን ተቃውሞና ከጭፍን ድጋፍ ነፃ በሆነ መንገድ ፖለቲካን በምክኒያታዊነት ማራመድ ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት - ከጥላቻ፣ ከስሜታዊና ከኩርፊያ ፖለቲካ ነፃ በሆነ መንገድ የመደማመጥ፣ የመቻቻል፣እውቅና የመስጠትና አብሮ የመስራት የፖለቲካ ባህልን ማራመድ ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት - ሌሎች የሰሩትን ሁሉ እያጥላሉና እያፈረሱ ከዜሮ ከመጀመር አስተሳሰብ ተላቆ ባለው ላይ በመገንባት መርህ መመራት ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት - እንደ አመችነቱ ቦታና ጊዜ እየመረጡ ሳይሆን የመደራጀት መብት ከአገሪቱ ህገ-መንግሥት እስካልተፋቀ ድረስ በማንኛውም ወቅትና ሁኔታ ሰላማዊ ትግልን ብቸኛ የትግል ስልት አድርጐ መታገል ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት - ለህግ የበላይነት፣ ለተቋሚት ግንባታና ለሂደት ልዩ ትኩረት በመስጠት የአገሪቱን ህጐችና ተቋሚት እያከበሩ ገንቢ ትችትና ተቃውሞ እያቀረቡ ሂደቱን የበለጠ የሚያጠናክር ትግል ማድረግ ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት - ለአገሪቱ ሁለንተናዊ ችግሮች መንግሥትንና ሌሎች የፖለቲካ ኃይሎችን ብቻ ተጠያቂ አድርጐ ማዬት ሳይሆን ሌሎችን ሆነ እራስን የአገሪቱ ችግሮችና መፍትሄዎች አካል አድርጐ ማዬት ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት - የህዝብን ጊዜያዊ ስሜት እያዩና ህዝብ ምን ለማዳመጥ ይፈልጋል እያሉ ጊዜያዊ ድጋፍ ሊያስገኝ የሚችል የእወደድባይነት ፖለቲካ ማራመድ ሳይሆን አገርንና ህዝብን እስከጠቀመ ድረስ እውነቱን ተናግሮ ከመሸበት የማደርን የሃቀኝነት ፖለቲካ ማራመድ ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት - ተቀናቃኝ ኃይልና በአጉል ፍረጃ፣ በስም ማጥፋትና በአሉባልታ ዘመቻ ሳይሆን በአጀንዳ ጥራትና በሃሣብ የበላይነት ታግሎ ማሸነፍ ማለት ነው፡፡

በአጠቃለይም ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት - በአገራችን ፖለቲካ የመንግሥት ሥልጣን በጠበንጃና በኃይል የሚያዘበት አዙሪት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተበጥሶ የኢትዮጵያ ህዝብ የሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር ባለቤት የሚሆንበትን አዲስና ወደኋላ የማይመለስ የፖለቲካ ባህል በአገራችን እንዲተከል ለማድረግ መታገል ማለት ነው፡፡

ኢዴፓን ከኢህአዴግም ሆነ ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተለዬ የዛሬውና የመጭው ትውልድ አዲስ የፖለቲካ ባህል ያለው ፓርቲ የሚያደርጉት ቁምነገሮች እነዚህ ከጥንፈኝነት ፖለቲካ የፀዱ የሦስተኛ አማራጭነት መርሆዎቹ ናቸው፡፡ በኢዴፓ እምነት የአሁኑ ትውልድ ካለፉት ትውልዶች ሁሉ የተሻለ በጐ ታሪክ ፈፅሞ ማለፍና ከራሱም በላይ የወደፊቱ ትውልድ ተጠቃሚ የሚሆንበትና የሚኮራበት ታላቅ ተግባር አከናውኖ ማለፍ ካለበት - የሚያዋጣው መንገድ እስካሁን በአገራችን ሲራመድ ከኖረውና ሁላችንንም ተሸናፊ ሲያደርገን ከቆዬው የፖለቲካ ባህል እራሱን አላቆ ይህንን ሦስተኛ የምክኒያታዊነት አማራጭ መከተል ነው፡፡

የዛሬውና የወደፊቱ የአገራችን ፖለቲካ ከእንግዲህ መመዘን ያለበትም -በስሜት፣ በጥላቻ፣ በአካባቢያዊ ወገንተኝነት፣ በጭፍን ተቃውሞና ድጋፍ፣ በትምህርት ደረጃ፣ በሃብት መጠንና በዕድሜ መሆኑ ቀርቶ በአማራጭ አስተሳሰብና አገራዊ አጀንዳ መሆን ካለበትም ከማንኛውም በአገራችን የሚገኝ ተቃዋሚ ፓርቲ፣ በግልፅ ሊታይ የሚችል ከኢህአዴግ የተለዬና የተሻለ አገራዊ አጀንዳ ያለው ፓርቲ ኢዴፓ ነው ብለን እናምናለን፡፡

- ኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመርን የሚያራምድና ለቡድን መብቶች ቅድሚያ የሚሰጥ የግራ ፖለቲካ አራማጅ ኃይል ሲሆን፣ ኢዴፓ የሊበራል ዴሞክራሲን መስመር የሚያራምድና ለግለሰብ መብቶች ቅድሚያ የሚሰጥ የመካከለኛ ቀኝ ዘመም ፖለቲካ አራማጅ ነው፡፡

- ኢህአዴግ የወቅቱ የአገራችን ህገ-መንግሥት ሙሉ በሙሉ ለአገሪቱ ጠቃሚና ሊሻሻል የማይገባው የተዋጣለት ሠነድ ነው ብሎ የሚያምን ሲሆን፣ ኢዴፓ የወቅቱ ህገ-መንግሥት በስራ ላይ እስካለ ድረስ ሊከበርና ልንገዛበት የሚገባን ሠነድ ቢሆንም፣ በውስጡ ለአገሪቱ አንድነትና የኢኮኖሚ ዕድገት የማይበጁ አንቀፆችን ያካተተ በመሆኑ ወደፊት እራሱ ህገ-መንግሥቱ በሚፈቅደው አግባብ በህዝብ ውሳኔ ሊሻሻል ይገባዋል ብሎ ያምናል፡፡

- ኢህአዴግ በዋናነት ቋንቋንና ብሔረሰብዓዊ ማንነትን መሠረት ያደረገ የፌደራል አደረጃጀትን የሚደግፍ ሲሆን፣ ኢዴፓ እንዲህ ዓይነቱ አደረጃጀት አገርን ይጠቅማል ብሎ ስለማያምን ከዚህ በተለዬ ታሪካዊ ትስስርን፣ የቆዳ ስፋትን፣ የህዝብ ብዛትን፣ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደሪዊ አመችነትንና ቋንቋ እንደየአካባቢው ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ ፌደራላዊ አደረጃጀትን ይደግፋል፡፡

- ኢህአዴግ የመገንጠልን መብት የሚፈቅደው አንቀፅ 39 በአገሪቱ ህገ-መንግሥት የተካተተ መሆኑ ለአገሪቱ አንድነት ዋስትና ነው ብሎ የሚያምን ሲሆን፣ ኢዴፓ እንዲህ ዓይነቱ አንቀፅ በአገሪቱ ህገ-መንግሥት መካተቱ የአገሪቱን የወደፊት ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል ነው ብሎ ያምናል፡፡

- ኢህአዴግ አገሪቱ ብቻ ሳትሆን ዜጎችም የፖለቲካ ፓርቲ ሲያቋቁሙ በብሄረሰብዓዊ ማንነታቸው መደራጀታቸውን የሚደግፍና የሚያበረታታ ሲሆን፣ ኢዴፓ ዜጎች በፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ሲደራጁ ብሔረሰብዓዊ ማንነታቸውን ሳይሆን በዋናነት ለአገሪቱ ያላቸውን አማራጭ አስተሳሰብ መሠረት ባደረገ ርዕዮተ-ዓለም ዙሪያ ሊደራጁ ይገባል ብሎ ያምናል፡፡

- ኢህአዴግ በአገሪቱ ፖለቲካ ትልቁ ችግር የማንነት ወይንም የብሔር ጭቆና ነው በሎ የሚያምን ሲሆን፣ ኢዴፓ በኢትዮጵያ ፖለቲካ የብሔር ጭቆና ከብዙ ችግሮች መካከል አንዱ እንጂ ዋናው ችግር አይደለም ብሎ ያምናል፡፡

- ኢህአዴግ በልማታዊ መንግሥትነት አስተሳሰቡ መንግሥት በአገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ የማይተካ ሚና አለው ብሎ የሚያምን ሲሆን፣ ኢዴፓ በህግ የተገደበ የመንግሥት ጊዜያዊ የኢኮኖሚ ተሳትፎን ደግፎ፣ ነገር ግን በአገሪቱ ኢኮኖሚ ወሳኝ ሚና ያለው መንግሥት ሳይሆን የግሉ ዘርፍ ነው ብሎ ያምናል፡፡

- ኢህአዴግ አገራችንን ወደ ዕድገት ሊያሸጋግራት የሚችለው እርሻ መር የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ነው ብሎ የሚያምን ሲሆን፣ ኢዴፓ አንዱ መሪ ሌላው ተመሪ ሆኖ ሳይሆን ሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች ተገቢና ተመጣጣኝ ትኩረት አግኝተው እርስ በርስ ተደጋግፈውና ተመጋግበው ለአገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተዋፅኦ የሚያበረክቱበትን ስትራቴጂ ይደግፋል፡፡

- ኢህአዴግ የአገሪቱ መሬት ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት መያዝ አለበት ብሎ የሚያምን ሲሆን፣ ኢዴፓ መሬት በግል፣ በወልና በመንግሥት ባለቤትነት እንዲያዝ የሚያስችል ሦስት ዓይነት የመሬት ስሪት መኖር አለበት ብሎ ያምናል፡፡

ከእነዚህ ግልፅና ዋና ዋና የፖለቲካና የኢኮኖሚ አስተሳሰብ ልዩነቶች በተጨማሪም በተለያዩ የአፈፃፀም ጉዳዮችና በሚያራምዱት የፖለቲካ ስልት ኢህአዴግና ኢዴፓ ግልፅ ልዩነት አላቸው፡፡ ኢዴፓ በወደፊቱ የአገሪቱ ፖለቲካ በማንኛውም ዜጋ መደገፍም ሆነ መነቀፍ ካለበት በተራ ወሬና ጭፍን ፍረጃ ሳይሆን በእነዚህ መሠረታዊ አገራዊ አጀንዳዎቹ መሆን ይገባዋል ብለን እናምናለን፡፡

ኢዴፓና ኢህአዴግ እንደማንኛውም በአንድ አገር ውስጥ የሚገኙ ሁለት ፓርቲዎች በመካከላቸው መሠረታዊ ልዩነቶች ቢኖሩዋቸውም፣ በሌላ በኩል የጋራ አገራዊ አጀንዳዎች ሊኖሯቸው ስለሚገባ ልዩነቶቻቸውን በአግባቡ ጠብቀው በጋራ አገራዊ ጉዳዬቻቸው ዙሪያ ግን አብረው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሁሉም በአገሪቱ የምንገኝ ፓርቲዎች እርስ በርስ በጠላትነት መተያዬታችንን አቁመን ቢያንስ በጋራ አገራዊ ጉዳዬቻችን አብረን መስራት የማንችል ከሆነ አስተማማኝ ሰላም ማግኘትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በዘላቂነት መገንባት ይቅርና አገራዊ ህልውናችንን ጠብቀን መቀጠላችንም አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

ሁለቱ ፓርቲዎች ማለትም ኢዴፓና ኢህአዴግ ከአገራዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አጀንዳዎች አንፃር ያሉአቸው ልዩነቶች እጅግ መሠረታዊና አገሪቱን በተለያዩ ሁለት አቅጣጫዎች ሊመሩ የሚችሉ በመሆናቸው በሁለቱ ፓርቲዎች መካከል ለፖለቲካ ሥልጣን ሊካሄድ የሚችለው ትግል ተፎካካሪዊና ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ ከኢህአዴግ አመለካከትና አቋም ይልቅ አገሪቱን ለዘላቂ ሰላም፣

ለእውነተኛ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓትና ለኢኮኖሚ ብልፅግና የሚያበቃው የኢዴፓ አመለካከትና አቋም ነው ብለን ስለምናምን ይህንን ዓላማችንን በአገራችን እውን ለማድረግ የሚያበቃንን መንግሥታዊ ሥልጣን በህዝብ ምርጫ እስከምናገኝ ድረስ ትግላችን ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ የአገራችን ችግሮች መንግሥትን በመለወጥ ብቻ ሊፈቱ የማይችሉ ጥልቅና ውስብስብ በመሆናቸው ምክኒያትም ትግላችን የመንግሥት ለውጥ ከማምጣትም በላይ በሁለንተናዊ መልኩ የራሱን ችግሮች በራሱ መፍታት የሚችል የበቃ ኀብረተሰብ በመፍጠር ዓላማ ላይ ትኩረት የሚሰጥ ይሆናል፡፡

ምርጫ 97ን ተከትሎ በአገራችን ፖለቲካ የተፈጠረው ችግር የትግሉን ሂደት ይበልጥ በማራዘም ረገድ የተጫወተው አሉታዊ ሚና ከፍተኛ ቢሆንም - ቀድሞውንም ሰላማዊ ትግልና የምርጫ ፖለቲካ በአገራችን ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዲደርስ የማይናቅ ሚና የተጫወተው ኢዴፓ፣ ዛሬም እንደ ትናንቱ ትግሉን ከሚገኝበት ድክመት አውጥቶ ወደተሻለ ደረጃ ለማድረስ ከፍተኛ ኃላፊነት ይጠበቅብኛል ብሎ ያምናል፡፡ ይዋል ይደር እንጂ በሂደት ይህንንም ኃላፊነቱን እውን እንደሚያደርገው ከልብ ይተማመናል፡፡ ይህንንም መሠረታዊ እምነት ይዞ ኢዴፓ በፖለቲካ ሂደቱ ዙሪያ ሊገጥሙት የሚችሉትን ፈተናዎች ሁሉ ተጋፍጦና ተቋቁሞ በአገራችን በ2002 ዓ.ም በሚካሄደው ብሔራዊ ምርጫ ለመሳተፍ ከወዲሁ በእርግጠኝነት ወስነናል፡፡ በሰላማዊ ትግል የፖለቲካ ሂደት ኩርፊያና ተስፋ መቁረጥ ቦታ የላቸውምና በዚች አገር ምክኒያታዊ ፖለቲካ ዳብሮና አድጐ ለድል እንዲበቃ የሚፈልጉ ዜጐች ሁሉ በሁለንተናዊ መልኩ ድጋፋቸውን እንዲያደርጉ በዚህ አጋጣሚ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

ኢዴፓ-የወደፊቱ ፓርቲ!

አመሰግናለሁ፡፡